# "ከህወሓት አንዳንድ አመራሮች በላይ
# ለትግራይ ህዝብ ጠላት የለም"

## አቶ ታደለ ደርሰህ የቪኢኮድ ዳይሬክተር

በይርጋ አበበ

አቶ ታደለ ደርሰህ የቪዥን ኢትዮጵያ ኮንግረስ ድርጅት (ቪኢኮድ) ዋና ዳይሬክተር ሲሆኑ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በግልጽ በመስጠት ይታወቃሉ። ለአገር እድገት ሶስት መሰረታዊ ነገሮች መሟላት አለባቸው የሚሉት አቶ ታደለ፤ የሶስቱን ተቋማት ማንነት ሲገልጹም <<ነጻ ሚዲያ፣ የማህበራት ጠንካራነት እና ነጻ የፍትህ ስርዓት>> ናቸው ይላሉ። አቶ ታደለ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ለሰንደቅ ጋዜጣ የሰጡትን አጠር ያለ ቃለ ምልልስ ከዚህ በታች አቅርበነዋል።

ሰንደቅ፡- ከ 1990 ዓ.ም ወዲህ በኢትዮጵያ እና ኤርትራ መካከል ያለው ግንኙነት ፍጹም ሰላም የራቀውና የሻከረ ሆኖ ቆይቷል። በቅርቡ የተጀመረውን የመሪዎችን ግንኙነትና የአገራትን የግንኙነት እንቅስቃሴ እንዴት ያዩታል?

አቶ ታደለ፡- በመጀመሪያም አላስፈላጊና ምክንያት የሌለው ጦርነት ነበር የተካሄደው። የአንድ እናት ልጆች ሁለት ወንድማማችና እህትማማች ህዝቦች መካከል የተካሄደ የመጠፋፋት ጦርነት ነበር። በዚያ <<ምክንያት አልባ ጦርነት>> የህይወት እና አካል መስዋዕት እንዲሁም አላስፈላጊ የንብረት ውድመት ያስከተለ ሲሆን ለዚያ ጦርነት መነሻ ምክንያት የነበሩ ሰዎች በታሪክም በህግም ተጠያቂ መሆናቸው አይቀርም። ከ 70 ሺህ በላይ ሰዎችን ያጠፋው ጦርነት ምንም እንኳን ለጊዜው የሁለቱን ህዝቦች ግንኙነት ቢያቋርጠውም ሁለቱ አገራትና ህዝቦቻቸው ግን ፈጽሞ የሚለያዩ አይደሉም።
ሁለቱ የማይነጣጠሉ ህዝቦች እንዲነጣጠሉ የተደረገው ከጦርነቱ በፊት ነው። ወደ ስልጣን እንደወጡ ለኤርትራዊያን ከኢትዮጵያ መገንጠል የቀረበላቸው የህዝበ ውሳኔ ምርጫ "ከነጻነትና ከባርነት" የሚል ነበር። በየትኛውም መመዘኛ ስናስበው አእምሮው የሚያገናዝብ ማንኛውም ሰው ከእነዚህ ጥያቄዎች "ባርነትን" ሊመርጥ አይችልም። ይህን ስንመለከት ከመጀመሪያውም ሁለቱ ህዝቦች እንዲለያዩ ሆን ተብሎ የታሰበ እና ኋላ ቀር ቃላትን ነበር የተጠቀሙት። ይህ የተደረገው ደግሞ ከጀርባው መሰሪ ተንኮሎች ስለነበሩ ያንን ለማስፈጸም የተደረገ ሴራ ነው።

ሰንደቅ፡- በሁለቱ አገራት መካከል የተካሄደውን ጦርነት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድን ጨምሮ በርካታ ሰዎች ያወግዙታል። ነገር ግን ከማውገዝ በዘለለ በህይወት ያሉትን ለጦርነቱ መነሻ ምክንያት የሆኑ ሰዎችን በህግ ተጠያቂ ለማድረግ አይቻልም? በህይወት የሌሉትስ በታሪክ ተጠያቂ ከመሆን አያመልጡም ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?

አቶ ታደለ፡- አንደኛ ምንም ቢሆን ምንም ታሪክን ማዛባት አይቻልም። የሁለቱ አገራት ጦርነት ሲካሄድ በወቅቱ የሚጠቀሙ አካላት ነበሩ፤ እነዚህ አካላት ደግሞ የሚጠቀሙትን ያህል ተጠቅመዋል። በታሪክ ግን ምን ጊዜም ቢሆን ተወቃሾች ናቸው። በታሪክ ተወቃሽ የሚሆኑበት ምክንያት ደግሞ እነዛ ለአገራቸው ሲሉ ህይወታቸውን የከፈሉ የ 70 ሺህ ኢትዮጵያዊያን አጽም ይፋረዳቸዋል። አላግባብ የወደመው ኢኮኖሚ ይፋረዳቸዋል፤ የኢትዮጵያ እና ኤርትራ ህዝብ አንድ መሆኑ ስለማይቀር የሁለቱ ህዝቦች በታሪክ ይፋረዷቸዋል። ይህ መሰሪ ተግባራቸው እስከመጨረሻው ድረስ የከፋት አሻራውን ይዞ ይቀጥላል።
ነገር ግን በህይወት ያሉት ለዛ ወንጀላቸው ማሰሪያ የሚሆናቸው ዘመኑ የይቅርታ እና የፍቅር ስለሆነ ማንም ሰው በታሪክ ይሳሳታል። እነዚህ ሰዎች የተሳሳቱት ስህተት፣ ከስህተት ሁሉ የገዘፈ ቢሆንም ለሰሩት ስራ ተጸጽተው የኢትዮጵያንና ኤርትራን ህዝብ

በግልጽ ይቅርታ ከጠየቁ የሁለቱም አገራት ህዝቦች የይቅርታ ህዝብ ስለሆኑ ይቅር ይሏቸዋል። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ለመጸጸትና ይቅርታ ለመጠየቅ ወኔ ሊኖራቸው ይገባል። ምንም ሳይደረግና የተፈጸመ ነገር ሳይኖር መስቀል አደባባይ ላይ አስወጥተው በሀሰት ያስጨፈሩን ሰዎች ናቸው። እነዚህ የህወሓት መሪዎች በህግም በታሪክም ተጠያቂ መሆን ያለባቸው ለዚህ ሁሉ ጥፋታቸው ነው። እዚህ ላይ ግን በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው የትግራይን ህዝብ ከህወሓት መሪዎች ለይቶ ማየት እንደሚኖርብን ነው።

ሰንደቅ፡- ህወሓትን እና የትግራይን ህዝብ ለይተን ማየት አለብን ብለዋል። ቀደም ሲል ዶክተር አብይ አህመድም ይህንኑ ብለውታል። ህወሓቶች ደግሞ የትግራይ ህዝብ እና ህወሓት አይነጣጠሉም ሲሉ ተናግረዋል። እርስዎ ሁለቱ ይለያያሉ ያሉበትን ምክንያት ያብራሩልን?

አቶ ታደለ፡- የትግራይ ህዝብ ትልቁ ጠላት ማንም ሳይሆን ህወሓት ነው። ከህወሓት መሪዎች በላይ ለትግራይ ህዝብ ጠላት የለም። ለዚህ ነው የትግራይ ህዝብን እና ህወሓትን ለይተን ማየት አለብን የምለው። ምክንያም ጥቂት የህወሓት አፈጮሌዎች እና ካድሬዎች ወይም ደካሞች ሰሩት ብለን የትግራይን ህዝብ አንጠላም። እንደመር ስንል የትግራይን ህዝብ ጨምረን ነው፤ እንደመር ስንል ትናንት ህዝቡን ያናከሱት የህወሓት መሪዎች ተጸጽተው ህዝብን ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው እያልን ነው። እነዚህ የህወሓት መሪዎች ለዚህ ጥፋታቸው በመጀመሪያ ደረጃ የትግራይን ህዝብ ይቅርታ መጠየቅ ይኖርባቸዋል።
ሰንደቅ፡- ኢትዮጵያ እና ኤርትራ ደም አፋሳሽ ጦርነት በኋላ አዲስ የግንኙነት ምዕራፍ ለመጀመር በመሪዎች ደረጃ ጥረት እየተካሄደ ነው። ዛሬም (ቃለ ምልልሱ በተካሄደበት እለት) ዶክተር አብይ ወደ አስመራ ተጉዘዋል። ነገር ግን ይህን የዶክተር አብይ እንቅስቃሴ የሚተቹ ፖለቲከኞች <<ግንኙነቱ ትግራይን ያላካተተ ስለሆነ ትርጉም አልባ ነው>> ይሉታል። ትግራዮች ያልተሳተፉበት ግንኙነት ሲባል ምን ማለት ነው?

አቶ ታደለ፡- ቀደም ብዬ እንደነገርኩህ እኮ ነው። <<ዛሬም ቢሆን ህወሓት የበላይ ነው። ስለዚህ የህወሓት መሰሪ ተግባር መቀጠል አለበት>> እያሉን ነው ያሉት። የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ የህወሓት መሰሪ ተግባር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቆም አለበት ነው እያለ ያለው። እነዚህ የህወሓት መሪዎች መሰሪነት የጀመረው እኮ አሁን አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ገና በ 1968 ዓ.ም ወደ ደደቢት በርሃ ሲወርዱ ባወጡት ማንፌስቶ ገጽ አራት ላይ <አማራ ጠላታችን ነው> ብለው አማራንና ትግራይን ያናከሱ ናቸው። ስለዚህ ያ መሰሪ ተግባራቸው ዛሬም እንዲቀጥል ነው የሚፈልጉት። ነገር ግን ያ መሰሪ ተግባራቸው የተቃጠለ ካርታ ነው፤ የትም ቦታ ሄዶ ሊሰራላቸው አይችልም። የትግራይ ህዝብ ዛሬ የሚፈልገው ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ወንድምና እህቶቹ ጋር በጋራ ሆኖ በዚህች አገር ላይ ሁሉም እኩል ተጠቃሚ ሆኖ መኖርን እንጂ፤ በጥይት መደባደብን እና በሌላው ጉዳይ መወነጃጀልን እንዲሁም አድማ እና የህወሓትን መሰሪ ተግባር መፈጸም እና ሰለባ መሆንን አይደለም።
የትግራይ ህዝብ እንደሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱን ያጣና በህወሓት መሰሪዎች ጭቆና የተረገጠ ህዝብ ነው። ንጹህ ውሃ ለማግኘት የተቸገረ እና የትምህርትም ሆነ የጤና አቅርቦት ያጣ ህዝብ ነው። እነዚህ የህወሓት መሰሪዎች <<የትግራይን ህዝብ እንወክላለን>> የሚሉት ህዝቡን እንደዚህ እየበደሉ ነገር ግን የትግራይን ህዝብ ከሌሎቹ ወንድምና እህቶቹ ጋር እንዲለያይ እያደረጉት ነው። ስለዚህ የትግራይ ህዝብ እነዚህን ሰዎች በጽኑ ታግሎ ከትከሻው ላይ ሊያወርዳቸውና ላደረሱበት በደልም በህግ ሊፋረዳቸው ይገባል።
እነዚህ በትግራይ ህዝብ ትከሻ ላይ ተቀምጠው 27 ዓመት ሙሉ በደልና ግፍ ሲፈጽሙብን የከረሙት የህወሓት አንዳንድ መሪዎች ለፈጸሙት ግፍ ተጸጽተው ይቅርታ ሊጠይቁ ብቻ ሳይሆን እነሱ ለጨቆኑት ህዝብ ነጻ እንዲወጣ የተመረጠው ዶክተር አብይም በፈርኦን ቤት ያደገ ሙሴ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል።

ሰንደቅ፡- ዶክተር አብይ አህመድ በፈርኦን ቤት ያደጉ ሙሴ ናቸው ለማለት ያስደፈረዎት ምንድን ነው?

አቶ ታደለ፡- ዶክተር አብይ ገና ከ 15 ዓመታቸው ጀምረው ያደጉት በጨቋኝና መሰሪ ከሆኑት ከህወሓት መሪዎች ጋር ቢሆንም፤ እሳቸው ግን ለህዝባቸው ነጻነት፣ ፍቅርና ሰላም መስበክ የቻሉ ሰው ስለሆኑ ነው። ገና ከ 15 ዓመታቸው ጀምረው እነዚህን ሰዎች

በሚገባ አይተዋቸው መሰሪነታቸውንም ተረድተው እና ይህ አካሄዳቸውም ለኢትዮጵያ እንደማያዋጣ ተረድተው ጊዜውን ጠብቀው የተነሱ ሰው ናቸው። እሳቸውን ለዚህ ህዝብ የላካቸውም እግዚአብሔር ነው።
በነገራችን ላይ ዶክተር አብይ የሚያስፈልጉት ለኢትዮጵያ ብቻ አይደለም፤ ለምስራቅ አፍሪካ እና ለአፍሪካም የሚያስፈልጉ ሰው ናቸው። እኛም ብንሆን እኒህን ጠቅላይ ሚኒስትር በማንኛውም በምንችለው መንገድ ሁሉ ልናግዛቸውና ልንተባበራቸው ይገባል ብዬ አስባለሁ። እነዚህ ሰዎች ግን (የህወሓት መሪዎችን) ይህን እውነታ መቀበል ካልቻሉ ሰውነታቸውም ያጠራጥረኛል። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ይህን መሰሪነታቸውን ካላቆሙ እንኳን ለኢትዮጵያ እና ለትግራይ ህዝብ ቀርቶ ለራሱ ለህወሓት እና ለራሳቸውም አይበጁም። ጊዜው መሽቶባቸዋል።

ሰንደቅ፡- ዶክተር አብይ አህመድና አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የጀመሩት ግንኙነት ለቀጠናውና ለሁለቱ አገራት የሚኖረው ትርጉም ምንድን ነው?

አቶ ታደለ፡- በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ ጉዳይ ይኖራል ብዬ የማስበው ጥቅም የሰው አእምሮ ሰላም ይሆናል። እናት ከልጇ፤ ባል ከሚስቱ፤ ወንድም ከወንድሙና እህት ከእህቷ ጋር ተለያይቶ ነው ላለፉት 27 ዓመታት የቆዩት። ስለዚህ እነዚህ መለያየት ያልነበረባቸው ህዝቦች አለመለያየታቸውን ያመጣል።
በሌላ ጎን ደግሞ <<የውሃ እናት>> እየተባለች የምትጠራውን አገር (ኢትዮጵያን ለማለት ነው) ወደብ አልባ ማድረግ በታሪክ ማንም ይቅር ሊለው የማይችል ወንጀል ነው። ስለዚህ አሁን የሁለቱ መሪዎች ግንኙነት ይህንን ወንጀል እንዲቀር ያደርገዋል። አሰብ የእኛ ንብረት ሆኖ ሳለ በንብረታችን መጠቀም እየቻልን በሌላ ቦታ እንድንጠቀም የተደረገው በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚ አሻጥር በመፈፀሙ ነው። ይህንንም ስለሚቃልል የመሪዎቹ መገናኘት ጠቀሜታ አለው።
ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ቦታው ስትራቴጂክ ነው። በዚህ ስትራቴጂክ ቦታ ላይየድርሻውን ለማግኘት የማይጠቀም አካል የለም። ብዙዎቹም አሰፍስፈው እየተጠባበቁ ነው። ስለዚህ ይህን የመሰለ ስትራቴጂክ ቦታ ሰላም እንዲሆን ማድረግ ለቀጠናው ሰላም ይሆናል። ምስራቅ አፍሪካ ሰላም ከሆነ ደግሞ መላ አህጉሩ ሰላም ይሆናል። ቀይ ባህር ሰላም ከሰፈነበት ዓለምም እንዲረጋጋ የራሱን ሚና ይጫወታል።
ከጦርነት ያተረፍነው ነገር ቢኖር ኪሳራችንን ማብዛት ብቻ ነው። እኛ ስንጣላ እነሱ (ምዕራባዊያንን) ለእኛ መሳሪያ ያቀብላሉ። እኛ በእነሱ ዘመን ያለፈበት መሳሪያ ስንተላለቅ <<የሰላም ኮንፈረንስ>> ብለው ይጠሩንና በሌላ አቅጣጫ አዳዲስ የጦር መሳሪያዎችን እያመረቱ እንደገና እንድንጫረስ ያደርጉናል። ስለዚህ ይህ እኩይ ተግባር በምስራቅ አፍሪካ እንዲቆም የሚያደርግ የግንኙነት ጅማሮ ነው ብዬ አስባለሁ።

ሰንደቅ፡- የወደብ ጉዳይ ካነሱ አይቀር ኢትዮጵያ ወደብ እንዲኖራት ከኢህአዴግ ውጭ ያሉ ፖለቲከኞች ደጋግመው ይናገራሉ። በኢህአዴግ በኩል ግን ከአቶ መለስ ዜናዊ ጀምሮ የፓርቲው ከፍተኛ መሪዎች የወደብ ጥያቄን የሚያነሱትን ሰዎች <<ጦርነት ናፋቂዎች>> ሲሉ ይወቅሷቸዋል። ቀደም ሲል የኢህአዴግ መሪዎች ወደብን ይገልጹበት ከነበረው እይታ ወጣ ባለ መልኩ ዶክተር አብይ የወደብን አስፈላጊነት ማቀንቀናቸው የኢህአዴግ እምነት ተቀይሯል ብለው ያስባሉ?

አቶ ታደለ፡- ይህ የኢህአዴግ እምነት ነው ብዬ አላስብም፤ አላንምም። የወደብ ጉዳይ የኢህአዴግ እምነት ቢሆንማ ኖሮ ታሪክ ወደፊት ዝርዝር ሁኔታውን ቢያወጣውም ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም መስቀል አደባባይ ላይ በተጠራ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ እንደዛ አይነት የህዝብን ስሜት የሚነካ ተግባር አይፈጸምም ነበር (ዶክተር አብይን ኢላማ ያደረገ የቦንብ ጥቃት መፈጸሙን)። የወደብ ጥያቄም የኢህአዴግ ፍላጎት አይደለም። የወደብ ጥያቄ ከኢህአዴግ ውጭ ያሉ ከመቶ ሚሊዮን በላይ ዜጎች የሚጠይቁት ጥያቄ ነው። ይህን የህዝብ ጥያቄ ደግሞ ኢህአዴግ መቀበል አለበት። ኢትዮጵያ ላይ ወደብ እንዳይኖራት የተፈረደባትም በኢህአዴግ በተለይም በህወሓት መሪዎች አማካኝነት ነው።